የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

# የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ ቃለ-ጉባዔ ናሙና (Template)

አዲስ አበባ
ሕዳር 2018 ዓ.ም

**__________.አ.ማ (በምስረታ ላይ ያለ)**

**<u>የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ</u>**

**<u>ቃለ ጉባዔ</u>**

1. **<u>ጠቅላላ ጉባዔ የተደረገበት ቀን፣ሰዓትና ቦታ</u>**

   ሀ. ቀን፡-____________________

   ለ. ሰዓት-፡____________________

   ሐ. ቦታ፡-____________________

2. **<u>የጉባዔው ጥሪ አደራረግ</u>**

   ይህ የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ የተጠራው በንግድ ሕግ አንቀጽ 262፣ አንቀጽ 367(___) እና አንቀጽ 370[1] መሰረት ከጉባዔው ዕለት 24 ቀናት አስቀድሞ ***<u>(አገር-አቀፍ/ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም ለእያንዳንዱ የአክሲዮን ፈራሚ ባስመዘገበው አድራሻ በተላከ ደብዳቤ ወይም ለዚሁ ዓላማ በሰጠው ኢሜይል ወይም ሌላ አስተማማኝ የኤሌክትሮኒክ ዘዴ)</u>***[2] አማካኝነት በማህበሩ አደራጅ ኮሚቴ ተጠርቷል፡፡

3. **<u>የጉባዔው ሰብሳቢ፣ድምጽ ቆጣሪዎች፣የጉባዔው ጸሐፊ፣ በጉባዔው የተገኙ አደራጆች እና ታዛቢዎች</u>**

   3.1 **<u>የጉባዔው ሰብሳቢ</u>**

   የማህበሩ የአደራጅ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም በጉባዔው ሰብሳቢው ካልተገኘ ምክትል ሰብሳቢ፣ምክትል ሰብሳቢ ካልተገኘ በጉባዔው የተመረጠው የአደራጅ ኮሚቴ አባል የጉባዔው ሰብሳቢ ሆኖ ጉባዔውን ስለመምራቱ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 379 መሠረት በቃለ-ጉባዔው በግልጽ መስፈር አለበት፡፡

   3.2 **<u>የጉባዔው ድምጽ ቆጣሪዎች እና የጉባዔው ጸሐፊ</u>**

   ጉባዔው ለመጀመር በንግድ ሕጉ አንቀጽ 380(1) መሰረት በጉባዔው በአክሲዮን ፈራሚነት ወይም በወኪልነት ከተገኙ እና ፈቃደኛ ከሆኑት_______ከፍተኛ የተፈረመ የአክሲዮን ድርሻ ባላቸው ፈራሚዎች መካከል በተደረገ ስምምነት ከዚህ በታች በተቀመጠው ሠንጠረዥ

---

[1] በንግድ ሕግ አንቀጽ 390 መሰረት ይህንኑ ስለፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ አጠራር የተመለከተውን የተለመደው ሥርዓት ሳይከተሉ ሁሉም የማህበሩ ፈራሚዎች ወይም ወኪሎቻቸው በስምምነት ጉባዔ በማካሄድ በሕግ አግባብ በፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣን ስር በሚወድቅ ማንኛውም ጉዳይ ላይ መወያየት እና ውሳኔ ማሳለፍ ይቻላል፡፡ ሆኖም ጉባዔው በዚህ አግባብ ስለመደረጉ በግልጽ በቃለ-ጉባዔው መገለጽ/መጻፍ አለበት፡፡

[2] ከእነዚህ በቅንፍ የተቀመጡ የጉባዔ ጥሪ ማድረጊያ ዘዴዎች መካከል አደራጅ ኮሚቴው ጉባዔውን ለመጥራት የተጠቀመው ዘዴ በግልጽ መጠቀስ አለበት፡፡ እንዲሁም የጉባዔው ጥሪ በማናቸውም ዘዴ ቢደረግም የጉባዔው ጥሪ የተደረገበት ሰነድ ግልባጭ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 264(1) መሠረት ከቃለ-ጉባዔው ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፤ካልሆነ ግን በቃለ-ጉባዔው ላይ ምንም ዓይነት ዝርዝር አስተያየት ወይም ማብራርያ ሳይሰጥ በመጣበት አግባብ ለአደራጅ ኮሚቴው ተመላሽ የሚደረግ ይሆናል፡፡ በተጨማሪ ለማሳያ የሚሆን የጉባዔው ጥሪ ማስታወቂያ ከዚህ የቃለ-ጉባዔ ናሙና ጋር ተያይዟል፡፡

የፈራሚዎች ቃለ-ጉባዔ ናሙና

ስማቸው የተዘረዘረው______ፈራሚዎች የጉባዔው ድምጽ ቆጣሪዎች ሆነው ተመርጠዋል[3]፡፡ እንዲሁም ማህበሩ በምስረታ ሂደት ሆኖ ቋሚ የማህበሩ ጸሐፊ መቅጠር ስለማይችል በአደራጅ ኮሚቴ አቅራቢነት በጉባዔው ተመርጦ ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ስሙ የተገለጸው ግለሰብ የጉባዔው ጸሐፊ ሆኖ ተሰይሟል፡፡

| ተ.ቁ | ስም | ኃላፊነት | በተወካይ ከሆነ የተወካይ ስም |
|---|---|---|---|
| 1. | | ድምጽ ቆጣሪ | |
| 2. | | ድምጽ ቆጣሪ | |
| 3. | | የጉባዔው ጸሐፊ | |

### 3.3 በጉባዔው የተገኙ የአደራጅ ኮሚቴ አባላት

| ተ.ቁ | ስም | ተወካይ | ኃላፊነት |
|---|---|---|---|
| 1. | | | ሰብሳቢ |
| 2. | | | ም/ሰብሳቢ (ካለ) |
| 3. | | | አባል |

### 3.4 በጉባዔው ያልተገኙ የአደራጅ ኮሚቴ አባላት[4]

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1. | | |
| 2. | | |

### 3.5 በጉባዔው የተገኙ ታዛቢዎች[5]

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | የወከላቸው ተቋም |
|---|---|---|
| 1. | | |
| 2. | | |

## 4. ምልዓተ ጉባዔ

4.1 ጠቅላላ የአክሲዮን ማህበሩ የፈራሚ አባላት ብዛት=____________________

4.2 ጠቅላላ የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ[6] የአክሲዮን ብዛት=____________________

4.3 በጉባዔው የተገኙት የማህበሩ ፈራሚዎች ብዛት______ሲሆኑ የፈረሙት የአክሲዮን ብዛትም_____________(_______%) ነው፡፡

---

[3] ከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻ ያላቸው ፈራሚዎች ድምጽ ለመቁጠር ፈቃደኛ ካልሆኑ ወይም በጉባዔ የተገኙት ፈራሚዎች ሌላ ሰው መምረጥ ከፈለጉ ጉባዔው እንደተጀመረ የድምጽ ቆጠራውን ለማድረግ የሚያስፈልጉ ድምጽ ቆጣሪዎች በንግድ ሕግ አንቀጽ 380(2) መሰረት የተወሰኑ ፈራሚዎችን መምረጥ ይችላሉ፡፡

[4] በጉባዔ ያልተገኙ የአደራጅ ኮሚቴ አባላት ከሌሉ(ሁሉንም የአደራጅ ኮሚቴ አባላት በጉባዔ ከተገኙ) ከዚህ የቃለ-ጉባዔው ንዑስ-ርእስ ቀጥሎ/ፊትለፊት ***"የለም"*** በማለት በአጭሩ ይገለጽ፤እንዲሁም ከስር የተቀመጠው ሠንጠረዥ መሠረዝ አለበት፡፡

[5] በጉባዔው የተገኙ ታዛቢዎች ካልነበሩ ከዚህ የቃለ-ጉባዔው ንዑስ-ርእስ ቀጥሎ/ፊትለፊት ***"የለም"*** በማለት በአጭሩ ይገለጽ፤ እንዲሁም ከስር የተቀመጠው ሠንጠረዥ መሠረዝ አለበት፡፡

[6] የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ በሚደረግበት ጊዜ በምስረታ ላይ ያለው ማህበር ጠቅላላ የተፈረመ ዋና ገንዘብ በሙሉ የተከፈለ ከሆነ ***"የተፈረመ እና የተከፈለ"*** ተብሎ መጻፍ አለበት፡፡

4.4 በጉባዔው ያልተገኙ የማህበሩ ፈራሚዎች ብዛት_____ሲሆኑ የፈረሙት የአክሲዮን ብዛት____________(______%) ነው፡፡

4.5 ጉባዔውን ለመጀመር አስፈላጊ የሆነ አነስተኛ የተፈረመ የአክሲዮን ብዛት____________ ወይም (______%) ነው፡፡

በንግድ ሕጉ አንቀጽ 262(2) እና አንቀጽ 402(___)[7] መሠረት ከጠቅላላ የተፈረመ የአክሲዮን ማህበሩ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) _____% የሚወክሉ ፈራሚዎች ስለተገኙ በጉባዔው አጀንዳዎች ላይ ተወያይተው ውሳኔ ለማሳለፍ ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ በድምጽ ቆጣሪዎች ተረጋግጦ ጉባዔው ቀጥሏል፡፡ በጉባዔው የተገኙትን ወይም ወኪል የላኩትን ፈራሚዎች ስምና አድራሻቸው፣ እያንዳንዱ ፈራሚ ያለውን የአክሲዮን መጠንና የሚሰጠው የድምፅ ቁጥር የሚያሳይ የጉባዔው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (Attendance Sheet) ከዚህ ቃለ-ጉባዔ ጋር አባሪ ሆኖ ተያይዞ ቀርቧል፡፡

## 5. የጉባዔ አጀንዳዎች[8]

5.1 የጉባዔው አጀንዳዎች ማጽደቅ[9]

5.2 አክሲዮን ማህበሩን ለማቋቋም የሚያስፈልጉ ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላታቸውን ተወያይቶ ውሳኔ ማሳለፍ፤

5.3 በአደራጅ ኮሚቴ ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ማሳለፍ፤

5.4 የአክሲዮን ማህበሩ የምስረታ ሂደት ኦዲት ሪፖርት ላይ ተወያይቶ መወሰን፤

5.5 በአክሲዮን ማህበሩ ረቂቅ መመስረቻ ጽሑፍ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ማሳለፍ፤

5.6 በዓይነት የተደረገ መዋጮ ካለ ግምቱን ተወያይቶ ማጽደቅ *(ከሌለ ከአጀንዳዎች ዝርዝር ውስጥ መሠረዝ አለበት)*፤

5.7 አደራጆች ለማህበሩ ምስረታ ያወጧቸውን ወጪዎች እና በገቡት ግዴታዎች ላይ ተወያይቶ መወሰን*(ከሌለ ከአጀንዳዎች ዝርዝር ውስጥ መሠረዝ አለበት)*፤

5.8 የአደራጅ ኮሚቴ የልዩ ጥቅም ልክ ተወያይቶ መወሰን፤

5.9 የአክሲዮን ማህበሩን የሚመሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ ማካሄድ፤

5.10 የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስለሚያስይዙት ዋስትና ተወያይቶ መወሰን *(አስፈላጊ ካልሆነ ከአጀንዳዎች ዝርዝር ውስጥ መሠረዝ አለበት)*፤

---

[7] እንደጉባዔው የጥሪ ዓይነት (በመጀመርያ፣ በሁለተኛ ወይም በሦስተኛ ጥሪ የተደረገ ጉባዔ ሊሆን ይችላል) የንግድ ሕግ አንቀጽ 402 አግባብነት እና ተቀባይነት ካለው ንዑስ-አንቀጽ ጋር መጠቀስ አለበት፡፡

[8] የፈራሚዎች ጉባዔ በምን ዓይነት አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ የማሳለፍ ስልጣን እንዳለው የሚያሳይ ተጨማሪ አጭር ማብራርያ (Brief Illustrative Note) ከዚህ የቃለ-ጉባዔ ናሙና ጋር ተያይዟል፡፡ በተጨማሪ እያንዳንዱ አጀንዳ በዚህ ንዑስ-ርእስ ሲጻፍ ይሁን ከዚህ በታች በንዑስ-ርእስ 6 የጉባዔው ውይይት አጭር ማጠቃለያ፣ የተሠጡትን ድምጾችና ውሳኔዎች ለማሳየት በድጋሚ በቅደም ተከተል በሚጻፍበት ጊዜ ምንም ዓይነት ቀላል ማሻሻያም ቢሆን ሳይደረግበት በጉባዔው ጥሪ ማስታወቂያ በተገለጸበት አግባብ በድጋሚ መጻፍ አለበት፡፡

[9] በጉባዔው ጥሪ ማስታወቂያ ላይ ይህ አጀንዳ ከመጀመሪያው ቢካተትም ባይካተትም በጉባዔው ውይይት የሚደረግባቸው አጀንዳዎች በባለአክሲዮኖች የጸደቁ ስለመሆናቸው በቃለጉባዔው በግለጽ መታየት አለበት፡፡ይሄውም ጉባዔው መጀመሪያ በጉባዔው ጥሪ ማስታወቂያ በተገለጹ አጀንዳዎች ብቻ ነው ወይይቶች አድርጎ ውሳኔዎች ያስተላለፈው ወይስ ጉባዔው በንግድ ሕግ አንቀጽ 372(2 እና 3) እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የሕግ ድንጋጌዎች በሚፈቅዱት መሠረት በተጨመሩ አጀንዳዎች ጭምር ውይይት በማድረግ ነው ውሳኔዎች ያስተላለፈ የሚለው ጉዳይ ቃለጉባዔ በራሱ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል መረጃ መያዝ አለበት፡፡

5.11 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሥራ ዋጋ ተወያይቶ መወሰን*(አስፈላጊ ካልሆነ ከአጀንዳዎች ዝርዝር ውስጥ መሠረዝ አለበት)*፤

5.12 የማህበሩ የውጭ ኦዲተር ሹመት ማካሄድ እና የሥራ ዋጋ ክፍያው ተወያይቶ መወሰን፤

5.13 ሌሎች ጉዳዮች[10]…………

5.14 የጉባዔውን ቃለጉባዔ ስለማጽደቅ[11]

6. <u>**የጉባዔው ውይይት አጭር ማጠቃለያ፣ የተሠጡትን ድምጾችና ውሳኔዎች**</u>

6.1 **አጀንዳ 5.1፡** አክሲዮን ማህበሩን ለማቋቋም የሚያስፈልጉ ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላታቸውን ተወያይቶ ውሳኔ ማሳለፍ፤

ሀ. የውይይት አጭር ማጠቃለያ

ለ. የተሰጡትን ድምጾች ውጤት እና ጉባዔው ያሳለፈውን ውሳኔ

6.2 **አጀንዳ 5.2፡** በአደራጅ ኮሚቴ ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ማሳለፍ፤

ሀ. የውይይት አጭር ማጠቃለያ

ለ. የተሰጡትን ድምጾች ውጤት እና ጉባዔው ያሳለፈውን ውሳኔ

6.3 **አጀንዳ 5.3፡**……………………………

ሀ. የውይይት አጭር ማጠቃለያ

ለ. የተሰጡትን ድምጾች ውጤት እና ጉባዔው ያሳለፈውን ውሳኔ

7. <u>**ለጉባዔው የቀረቡ ሰነዶች**</u>[12]

7.1 የፈራሚዎች ጉባዔ ጥሪ የተደረገበት ዘዴ እና ይዘት የሚያሳይ የጉባዔው የጥሪ ማስታወቂያ ጋዜጣ/ደብዳቤ/ኢሜይል_______ ገጽ ግልባጭ/ፕሪንትአውት፡፡

7.2 በአክሲዮን ማህበሩ የአደራጅ ኮሚቴ የተዘጋጀ ሪፖርት_______ ገጽ፡፡

7.3 የአክሲዮን ማህበሩ የምስረታ ሂደት ኦዲት ሪፖርት _______ ገጽ፡፡

7.4 በ____________ ቋንቋ የተዘጋጀ የአክሲዮን ማህበሩ ረቂቅ የመመስረቻ ጽሑፍ_______ ገጽ፡፡

---

10 በዚህ ስር ሊጨመሩ የሚችሉት አጀንዳዎች በጉባዔው ጥሪ ማስታወቂያ ባይነገሩም በፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔው ቀን ጉባዔው በአጀንዳነት ይዞ ተወያይቶ ውሳኔ ሊሰጥባቸው የሚችሉ ለምሳሌ ጉባዔው ሥራ ከመጀመሩ በፊት በስብሰባው ላይ ከተገኙት ፈራሚዎች መካከል በጉባዔው ላይ የተደረገው ውይይት እና የተላለፈው ውሳኔ በትክክል በቃለ-ጉባዔ ስለመስፈሩን አረጋግጠው በጉባዔው በተመረጡና በአካል በተገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና በጉባዔው ጸሐፊ ምትክ የሚፈርሙ ፈራሚዎች በንግድ ሕግ አንቀጽ 387(2) መሰረት መምረጥን ወዘተ…የሚመለከት እና ሌሎች በሕግ አግባብ በግልጽ የተፈቀዱ ጉዳዮች ካልሆኑ በስተቀር ሌሎች በጉባዔው ቀን የሚጨመሩ አጀንዳዎችም ሆነ በአጀንዳዎች ላይ የሚተላለፉ ውሳኔዎች ሕጋዊ ተቀባይነት እንደማይኖራቸው መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

11 በጉባዔው ውይይት ተደርጎባቸው የተወሰኑ ውሳኔዎች ባለአክሲዮኖች በተስማሙበት አግባብ በቃለጉባዔው የተመዘገቡ ስለመሆናቸው በድምጽ ማረጋገጫ እንዲሰጡበት ቢደረግ በኃላ ውሳኔዎቹን ባለመቀበል ውድቅ እንዲደረጉ የሚቀርብ አቤቱታዎችን ለመቀነስ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

12 በንግድ ሕግ አንቀጽ 264(1) መሠረት ለፈራሚዎች ጉባዔ የቀረቡትን ሰነዶች ዝርዝር በመግለጽ ከቃለ-ጉባዔው ጋር አባሪ አድርጎ ማያያዝ እና ስለመያያዛቸውም በቃለ-ጉባዔው ላይ መገለጽ አለበት፡፡

7.5 በዓይነት ለማህበሩ የተደረገ መዋጮ የሚያሳይ የባለሙያ ግምት አጭር መግለጫ/ሪፖርት_______ ገጽ፤ እንዲሁም በአደራጆችና በምስረታ ኦዲተር ስለግምቱ ትክክለኛነት የተሰጠ ማረጋገጫ ሰነድ_______ ገጽ፡፡

7.6 …………………

8. **በጉባዔው የተመረጡ እና በአካል የተገኙ የአክሲዮን ማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና የጉባዔው ጸሐፊ ማረጋገጫ**

እኛ የ__________________አክሲዮን ማህበር (በምስረታ ላይ ያለው) በፈራሚዎች ጉባዔ የተመረጥን እና በጉባዔው የተገኘን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና የጉባዔው ጸሐፊ ከዚህ ቃለ-ጉባዔ ሰነድ ጋር አባሪ ሆኖ የተያያዘው የጉባዔው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (Attendance Sheet) ላይ በየስማቸው የፈረሟቸው እና የከፈሏቸው አክሲዮኖች ብዛት በስማቸው አንጻር በተመለከቱት ትይዩ የፈረሙ ፈራሚዎች ወይም ተወካዮቻቸው_____________ቀን 201_____ዓ.ም በተካሄደው የማሕበሩ የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ ላይ መገኘታቸውንና ራሳቸው ወይም ወኪሎቻቸው በዚህ ቃለ-ጉባዔ ሠነድ ላይ የተገለጹትን ውሳኔዎች ማሳለፋቸው በንግድ ሕግ አንቀጽ 264(1) መሠረት በሙሉ ስምና ፊርማችን እያረጋገጥን፣ በሰነዶቹ ላይ ስለተገለጹት ጉዳዮች እና ስለተላለፉ ውሳኔዎች ትክክለኛነት ስማቸው በሰነዶቹ ላይ በተዘረዘሩት ሰዎችም ሆነ በሌላ በጉዳዩ ያገባኛል በሚል ወገን ለሚነሳ ማናቸውም የመብት ጥያቄ ኃላፊዎች መሆናችንን ጭምር እናረጋግጣለን፡፡

| ተ.ቁ | በጉባዔው የተመረጡ እና በአካል የተገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና የጉባዔው ጸሐፊ ስም ዝርዝር | ኃላፊነት | ፊርማ (በተወካይ ከሆነ የተገኘው የተወካይ ስም ይጻፍ) |
|---|---|---|---|
| 1. | | | |
| 2. | | | |
| 3. | | የጉባዔው ጸሐፊ | |

9. **የአክሲዮን ማህበሩ አደራጅ ኮሚቴ አባላት ማረጋገጫ**[13]

እኛ የ__________________አክሲዮን ማህበር (በምስረታ ላይ ያለው) የአደራጅ ኮሚቴ አባላት ከዚህ ቃለ-ጉባዔ ሰነድ ጋር አባሪ ሆኖ የተያያዘው የጉባዔው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (Attendance Sheet) ላይ በየስማቸው የፈረሟቸው እና የከፈሏቸው አክሲዮኖች ብዛት በስማቸው አንጻር በተመለከቱት ትይዩ የፈረሙ ፈራሚዎች ወይም ተወካዮቻቸው_____________ቀን 201_____ዓ.ም በተካሄደው የማህበሩ የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ ላይ መገኘታቸውንና ራሳቸው ወይም ወኪሎቻቸው በዚህ ቃለ-ጉባዔ ሰነድ ላይ የተገለጹትን ውሳኔዎች ማሳለፋቸውን በንግድ ሕግ አንቀጽ 264(1) መሠረት በሙሉ ስምና ፊርማችን እያረጋገጥን፣ በሰነዶቹ ላይ ስለተገለጹት ጉዳዮች እና ስለተላለፉ ውሳኔዎች ትክክለኛነት ስማቸው በሰነዶቹ ላይ በተዘረዘሩት ሰዎችም ሆነ በሌላ በጉዳዩ ያገባኛል በሚል ወገን ለሚነሳ ማናቸውም የመብት ጥያቄ ኃላፊዎች መሆናችንን ጭምር እናረጋግጣለን፡፡

| ተ.ቁ | የአደራጅ ኮሚቴ አባላት ስም ዝርዝር | ኃላፊነት | ፊርማ (በተወካይ |
|---|---|---|---|

[13] በዚህ ንዑስ-ርዕስ ስር የሚሰጠው የአደራጅ ኮሚቴ አባላት ማረጋገጫ በጉባዔ የተገኙት እንዲሁም የኮሚቴው አባል ሆነው እስከቀጠሉ ድረስ ያልተገኙትንም በሙሉ የሚመለከት ስለመሆኑ በአጽንኦት መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

| | | | ከሆነ የተገኘው የተወካይ ስም ይጻፍ) |
|---|---|---|---|
| 1. | | ሰብሳቢ | |
| 2. | | ም/ሰብሳቢ | |
| 3. | | ጸሐፊ | |
| 4. | | አባል | |

የፊርማዎች ቃለ-ጉባዔ ናሙና

## __________.አ.ማ (በምስረታ ላይ ያለ)

## የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ

## የጉባዔው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ

| ተ.ቁ | የፈራሚው ሙሉ ስም | አድራሻ[14] | | | | ያለውን የአክሲዮን መጠን | | የሚሰጠውን የድምጽ ቁጥር[15] | ፊርማ | ፈራሚው ለጉባዔው ተወካይ ከላከ የተወካዩን ስምና ፊርማ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ክልል | ከተማ | ቀበሌ | የቤ/ቁጥር | የተፈረመ | የተከፈለ | | | |
| 1. | | | | | | | | | | |
| 2. | | | | | | | | | | |

### የፈራሚዎች ጉባዔ ጸሐፊ ማረጋገጫ

እኔ የ_____________________________አክሲዮን ማሕበር(በምስረታ ላይ ያለ) የጉባዔው ጸሐፊ ከዚህ ቃለ-ጉባዔ ጋር አባሪ ሆኖ በተያያዘው የጉባዔ ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (Attendance Sheet) ላይ_______________ቀን 201___ዓ.ም በተካሄደው የአክሲዮን ማህበሩ የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ በጉባዔው የተገኙትን ፈራሚዎች ወይም ወኪሎች በየስማቸው ትይዩ የተጻፈው ስምና አድራሻቸው፣ እያንዳንዱ ፈራሚ ያለውን የአክሲዮን መጠንና የሚሰጠው የድምፅ ቁጥር በትክክል የተገለጸ ስለመሆኑ አረጋግጠው የፈረሙበት ስለመሆኑ በንግድ ሕግ አንቀጽ 378(2) መሠረት በስሜና ፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ሙሉ ስም:________________________

ፊርማ:______________

ቀን:______________

[14] በዚህ የፈራሚዎች አድራሻ ሥር ሊካተቱ የሚችሉ የፈራሚዎች ዝርዝር መረጃዎች ምስረታ ላይ ባለው የአክሲዮን ማህበሩ ምርጫ ለዚህ ዓላማ ብቻ ሊለያይ የሚችል ቢሆንም በምስረታ ላይ ያለው የአክሲዮን ማህበሩ መካተት አለባቸው ብሎ የወሰናቸው የፈራሚዎች ዝርዝር አድራሻ የሚገልጹ የሁሉም ፈራሚዎች መረጃዎች ግን በአግባቡ ተሟልተው መቅረብ አለባቸው፤ ምንም ዓይነት ያልተሟላ መረጃ ሊኖር አይገባም፡፡

[15] በመርህ ደረጃ ፈራሚዎች በጉባዔው የሚሰጡት ድምጽ ካላቸው የተፈረመ የአክሲዮን ድርሻ እኩል ስለመሆኑ ግምት የሚወሰድ ቢሆንም፤ ይህንኑ ግምት በተለይ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 264(3) እና አንቀጽ 271 መሠረት ሊገደብ ወይም ለውሳኔ በቀረበው አጀንዳ መሠረት ሊለያይ ስለሚችል እያንዳንዱ በጉባዔው የተገኘው ፈራሚ የሚሰጠው የድምጽ ቁጥር በዚህ የሠንጠረዡ አምድ(Column) ተሟልቶ ካልቀረበ የጉባዔው ውሳኔዎች ውጤት አልባ እንዲሆኑ በማድረግ ጉባዔው እስከ ማስደገም የሚደርስ አላስፈላጊ ውጤት እንዳያስከትል መረጃው በከፍተኛ ጥንቃቄ እና በትክክል ተሟልቶ መቅረብ አለበት፡፡

የፈራሚዎች ቃለ-ጉባዔ ናሙና

## 1ኛ ማሳሰቢያ

ከዚህ በላይ በተገለጸው አግባብ እንዲዘጋጅ የሚፈለገው የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ የቃለ-ጉባዔ ናሙና የተለያዩ ክፍሎች ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ታስበው በግርጌ ማስታወሻ *(foot notes)* የተጻፉ ማብራርያዎች ከቃለ-ጉባዔው የመጨረሻ ረቂቅ ሰነድ ተሠርዝው ንጹህ የሆነ ሰነድ ብቻ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንደሚቀርብ በጥብቅ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## 2ኛ ማሳሰቢያ

የአክሲዮን ማህበሩ ምስረታ በንግድ ሕግ አንቀጽ 252 መሠረት የተወሰኑ ሰዎች የአክሲዮን ሽያጩ ለሕዝብ ክፍት ሳያደርጉ ሙሉውን ዋና ገንዘቡ በራሳቸው ፈርመው በመክፈል የሚመሰረቱት ከሆነ ከዚህ በላይ በተገለጸው አግባብ እንዲዘጋጅ በታሰበው የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ ውስጥ “አደራጅ ወይም (የ)አደራጅ ኮሚቴ (አባላት)” የሚለው ቃል/ሀረግ “መስራች” በሚል እንዲሁም “ፈራሚ፣የፈራሚዎች ጉባዔ ወይም ከዚሁ ጋር በመያያዝ” የተጠቀሰው ቃል/ሀረግ “መስራች ወይም የመስራቾች ጉባዔ ወይም ከዚሁ ቃል በመያያዝ” ቃሉን/ሀረጉን ተክቶ ቃለ-ጉባዔው ተስተካክሎ መቀረጽ አለበት፡፡ ከዚህ ውጭ በንግድ ሕግ አንቀጽ 248 መሠረት የአክሲዮኑ ሽያጭ ለሕዝብ ክፍት በማድረግ በተመሰረተ የአክሲዮን ማህበር የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ ቃለ-ጉባዔ ወይም የመመስረቻ ጽሑፍ ላይ “መስራች ወይም መስራቾች”፣“የመስራቾች ወይም የመስራቾች ጉባዔ” ወዘተ… የሚሉ ቃላትና ሐረጋት መጠቀም ፍጹም ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ በትኩረት መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

የፈራሚዎች ቃለ-ጉባዔ ናሙና

## <u>የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ</u>

በንግድ ሕግ አንቀጽ 262 መሠረት ምስረታ ላይ ያለው የአክሲዮን ማህበር የምስረታ ኦዲት ከተጠናቀቀ በኋላ የአክሲዮን ማህበሩ አደራጆች ወዲያውኑ የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ መጥራት እንዳለባቸው እና ይህንኑ የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ **በሕግ በልዩ የተሰጠው ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቀ ሆኖ** የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በሚጠራበትና እና በሚመራበት አግባብ መፈጸም እንዳለበትም ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም የጉባዔው ምልአተ-ጉባዔ እና ውሳኔ ለመስጠት የሚያስፈልግ የድምጽ ብልጫም የሚሰላው የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በሚሰላበት መንገድ ስለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በዚህም መሠረት፡-

**<u>ምልዓተ ጉባዔ</u>**

❖ በንግድ ሕግ አንቀጽ 402(4) መሠረት የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ ምልዓተ ጉባዔ ተሟልቷል የሚባለው፡-
  - ሀ. በመጀመርያው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው ፈራሚዎች ውስጥ ቢያንስ የማህበሩን ዋና ገንዘብ አንድ ሦስተኛ (33.34%) የሚወክሉ ፈራሚዎች ወይም ወኪሎቻቸው በጉባዔው የተገኙ እንደሆነ ነው፡፡
  - ለ. በሁለተኛው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው ፈራሚዎች ውስጥ ቢያንስ የማህበሩን ዋና ገንዘብ አንድ አራተኛ (25%) የሚወክሉ ፈራሚዎች ወይም ወኪሎቻቸው በጉባዔው የተገኙ እንደሆነ ነው፡፡
  - ሐ. በሶስተኛ ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው የፈራሚዎች አክሲዮን የሚወክሉት ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ግምት ውስጥ ሳይገባ ፈራሚዎች ወይም ወኪሎቻቸው የተገኙ እንደሆነ ነው፡፡

**<u>ውሳኔ ለመስጠት የሚያስፈልግ ድምፅ</u>**

- ➢ በፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ በአጀንዳዎች ላይ ውሳኔዎች የሚተላለፉት በንግድ ሕግ አንቀጽ 402(1) መሠረት በጉባዔ በተገኙት ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው አክሲዮኖች ከወከሉት ካፒታል ሁለት ሦስተኛውን (66.67%) በሚወክሉት የፈራሚዎች ድምጽ (**Qualified Majority**) ከተደገፈ ነው፡፡
- ➢ በተጨማሪ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 264(4) መሠረት በፈራሚዎች ጉባዔ በሙሉ ድምጽ ተቀባይነት ካላገኘ በስተቀር፣ በረቂቅ መመስረቻ ጽሑፍ ላይ መሠረታዊ ለውጥ ማድረግ አይቻልም፣ ሆኖም በዓይነት የተደረገ መዋጮን ግምት ወይም ለአደራጆች ከትርፍ ድርሻ ላይ የሚሰጠውን ልዩ ጥቅም የሚመለከት የማሻሻያ ሀሳብ በጉባዔው በድምጽ ብልጫ ሊወሰን ይችላል፡፡

**<u>የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር</u>**

በዋናነት በንግድ ሕግ አንቀጽ 263 እንደተደነገገው የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. **አክሲዮን ማህበሩን ለማቋቋም የሚያስፈልጉ ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላታቸውን የማረጋገጥ፣** በዚህ አጀንዳ ርእስ-ጉዳይ ስር ቢያንስ፡-

- ❖ አደራጆች የአክሲዮን ማህበሩን ለመመስረት በሕጉ የተቀመጠውን የአደራጅነት መስፈርት የሚያሟሉ ስለመሆናቸው እና አክሲዮን ማህበሩን ለመመስረት በሚመለከተው የመንግስት ተቆጣጣሪ አካል የመጀመርያ ደረጃ ይሁንታ የተሰጣቸው ስለመሆኑ፤
- ❖ የሚመሠረተው የአክሲዮን ማህበር ስም ለማህበሩ መጠርያ እንዲሆን በሚመለከተው የመንግስት አካል ተመዝግቦ ይሁንታ የተሰጠው ስለመሆኑ፤
- ❖ ማህበሩን ለማቋቋም የሚያስፈልገው አነስተኛ የፈራሚዎች ቁጥር እንዲሁም የተከፈለ እና የተፈረመ ካፒታል በሕጉ አግባብ ስለመሟላቱ፣
- ❖ አክሲዮን ማህበሩን ለመመስረት አክሲዮን ለመግዛት ከፈረሙ ሰዎች የተሰበሰበው ዋና ገንዘብ በትክክል በማህበሩ ስም በተከፈተው ዝግ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ ተደርጎ የሚገኝ ስለመሆኑ፣ እንዲሁም የአገልግሎት ክፍያ መዋጮ ከፈራሚዎች ከተሰበሰበ ስለአጠቃቀሙ በውጭ ኦዲተር የተረጋገጠ የሂሳብ መግለጫ ስለመኖሩ፤
- ❖ የፈራሚዎች ጉባዔ ጥሪ በሕግ አግባብ ለሁሉም ፈራሚዎች ተደራሽ በሚሆን መንገድ/ዘዴ ጥሪ ስለመደረጉ፤ወዘተ.....

በማረጋገጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

2. **የአክሲዮን ማህበሩ ረቂቅ የመመስረቻ ጽሑፍ ተወያይቶ የማጽደቅ፤**
   - ❖ ረቂቅ መመስረቻ ጽሑፉ ቢያንስ በንግድ ሕግ አንቀጽ 255 ስር የተጠቀሱት ርዕሰ-ጉዳዮች የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ያካተተ ስለመሆኑ ጉባዔው መርምሮ እና ተወያይቶ ማጽደቅ አለበት፡፡
3. **በአክሲዮን ማህበሩ አደራጆች ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ማሳለፍ፤**
   - ❖ ይህ የአደራጆች ሪፖርት የአክሲዮን ማህበሩ የምስረታ ሂደት ከመጀመርያ እስከ ጉባዔው የተደረገበት ጊዜ የነበረውን አንኳር አንኳር ጉዳዮች የሚዳስስና የሚሸፍን መሆን አለበት፡፡ እንደ ሪፖርቱ ስፋትና ጥልቀት ይህንኑ ክፍል የራሱ ንዑስ-ርእስ ተሰጥቶት በተራ ቁጥር 1 ላይ ተካቶ ሊቀርብ ይችላል፡፡
4. **በአክሲዮን ማህበሩ የምስረታ ሂደት ኦዲት ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ማሳለፍ፤**
   - ❖ ይህንኑ የምስረታ ሂደት ኦዲት ሪፖርት ከፋይናንስ ነክ ውጭ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 261(2ሀ-ሠ) ስር የተዘረዘሩ ጉዳዮች ከበቂ ማብራርያ ጋር በራሳቸው ንዑስ-ርእስ ስር ማረጋገጫ የማይሰጥ ከሆነ ሙሉውን የጉባዔው ውሳኔዎች ውድቅ ተደርጎ ጉባዔው በድጋሚ እንዲደረግ የሚታዘዝ ስለመሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡
5. **ለአክሲዮን ማህበሩ በዓይነት የተደረገ መዋጮ ካለ ግምቱን የማጽደቅ፤**
   - ❖ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 257(1-4) ስር በተደነገገው ስርዓትና ቅደም-ተከተል መሠረት በትክክል ተከናውኖ ለጉባዔው ቀርቦ መወሰን አለበት፡፡
6. **አደራጆች ለማህበሩ ምስረታ ያወጡትን ወጪዎች እና የገቡት ግዴታዎች ካለ የማጽደቅ፤**
   - ❖ በማህበሩ የምስረታ ሂደት አደራጆች የገቧቸው ግዴታዎች ወይም ያወጧቸው ወጪዎች (ከራሳቸው ከኪሳቸውም ይሁን ከፈራሚዎች የአገልግሎት ክፍያ የተሰበሰበ ገንዘብም ይመለከታል) ለማህበሩ ምስረታ አስፈላጊ ስለመሆናቸው በምስረታ ኦዲት ተረጋግጦ ጉባዔው ከተቀበለው የአክሲዮን ማህበሩ አደራጆች ከሚያቀርቡት ሪፖርት ተለይቶ በራሱ

አጀንዳ ተይዞ ውይይት ተደርጎበት ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል፡፡ ካልሆነ ግን ግዴታውም ሆነ ወጪው አደራጆች በግላቸው ኃላፊነት የሚወስዱበት ይሆናል፡፡

7. **የአደራጅ ኮሚቴ የልዩ ጥቅም ልክ ተወያይቶ የመወሰን፤**
   - በንግድ ሕጉ አንቀጽ 253(1) መሠረት አደራጆች የአክሲዮን ማህበሩ ትርፍ ማግኘት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ከማህበሩ የተጣራ ትርፍ ከሃያ በመቶ ያልበለጠ ልዩ ጥቅም ከሦስት ዓመታት ሳልበለጠ ጊዜ ሊከፈላቸው እንደሚችል እና የክፍያው መጠን፣ ክፍያ የሚፈጸምባቸው ዓመታት አመራረጥ እና መሰል ዝርዝር ሁኔታዎች በመመስረቻ ጽሁፉ ከመደንገጉ በተጨማሪ ለብቻው ተወያይቶ ለመወሰን በአጀንዳ ተይዞ ውይይት ተደረጎበት በፈራሚዎች ጉባዔ ቃለ-ጉባዔ በድጋሚ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ካልሆነ ግን መመስረቻ ጽሑፉ ሲጸድቅ በእያንዳንዱ የመመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ እና ንዑስ-አንቀጽ በጉባዔው ለፈራሚዎች ማብራርያ እና በቂ የመወያያ ዕድል እንደተሰጠ የሚያሳይ የጉባዔ ተንቀሳቃሽ ምስል (**Video**) ከቃለ-ጉባዔው ጋር ተያያዞ መቅረብ አለበት፡፡

8. **የአክሲዮን ማህበሩን የሚመሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ ማካሄድ፤**
   - በንግድ ሕጉ አንቀጽ 298(1) ላይ የመጀመርያዎቹ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በመመስረቻ ጽሑፍ መሠረት ሊሾሙ እንደሚችሉ እና ሹመቱ እንዲጸድቅም ለፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ መቅረብ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ሆኖም በዚህ አግባብ የሚሾሙ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በዚሁ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (4) መሠረት ለእያንዳንዱ ተመራጭ/ዕጩ ተሿሚ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል በተናጠል በሚስጥር ድምጽ በመስጠት ስለመሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡ ካልሆነ ግን ውሳኔው ውጤት አልባ እንደሚሆን ግልጽ ሊሆን ይገባል፡፡

9. **የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስለሚያስይዙት ዋስትና የመወሰን፤**
   - የአክሲዮን ማህበር የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ሆነው የሚመረጡ ሰዎች የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና እንዲያስዙ በመመስረቻ ጽሑፍ እንዲካተት ማድረግ ግዴታ አይደለም፤ሆኖም በመመስረቻ ጽሑፉ እንዲካተት ከተወሰነ ግን በዚህ አጭር የማብራርያ ጽሑፍ ከላይ በተራ ቁጥር 7 በተገለጸበት አግባብ አካሄዶች በጉባዔውም ጭምር በድጋሚ ማረጋገጥ አስፈላጊ ጉዳይ ስለመሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

10. **ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሚከፈል የሥራ ዋጋ የመወሰን፤**
    - ይህንኑ አጀንዳ በተመለከተ የባንክ እና የኢንሹራንስ የአክሲዮን ማህበራት የሚመለከት ከሆነ **"ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሚከፈለው ወርሀዊ አበል"** ተብሎ ውይይት ተደርጎበት መወሰን እንዳለበት፤እንዲሁም ከእነዚህ የፋይናንስ ድርጅቶች ውጭ ለሚቋቋሙ የፋይናንስ ድርጅቶች ከሆነ ደግሞ **"ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሚከፈለው ዓመታዊ የሥራ ዋጋ"** በሚል የአጀንዳ ርእስ ጉዳይ ውይይትና ውሳኔ መሠጠት እንዳለበት ለሁሉም ግልጽ ሊሆን ይገባል፡፡

11. **የማህበሩ የውጭ ኦዲተር ሹመት ማካሄድ እና የሥራ ዋጋ ክፍያው የመወሰን፤**
    - ከንግድ ሕግ አንቀጽ 343(4)፣አንቀጽ 344(1) እና አንቀጽ 347 ድንጋጌዎች ይዘት ላይ በቀላሉ ለመገንዘብ እንደሚቻለው የአክሲዮን ማህበሩ የውጭ ኦዲተር ሹመት ማካሄድ እና የሥራ ዋጋ ክፍያ መወሰን የፈራሚዎች ጉባዔ ስልጣን ስለመሆኑ እና ስልጣኑ

በውክልናም ይሁን ለሌሎች የማህበሩ የአመራር አካላት የማይተላለፍ ስለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ስለሆነም የኦዲተሩ ሹመት እና የሥራ ዋጋው ክፍያ በፈራሚዎች ጉባዔ ካልተወሰነ በጉባዔው መሠየም ያለባቸውን የማህበሩ የአስተዳደር አካላት በሙሉ በሕጉ መሠረት አልተሰየሙም በሚል ድርጅቱ ከመቋቋም ሊያዘገየው ወይም ሊያደናቅፈው እንደሚችል ለሁሉም ግልጽ ሊሆን ይገባል፡፡

**ኢብባ/ሕአዳ**

የፈራሚዎች ቃለ-ጉባዔ ናሙና

## አባሪ-1

## <u>የጉባዔ ጥሪ ማስታወቂያ ናሙና</u>

## ___________________________አክሲዮን ማህበር (በምስረታ ላይ ያለ)

## <u>የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ የጉባዔ ጥሪ</u>

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የንግድ ሕግ አንቀጽ 262፣አንቀጽ 367፣ አንቀጽ____እና አንቀጽ 370 መሠረት የ____________________አክሲዮን ማህበር የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ____________________ቀን 201______ ዓ.ም ከ______ ሰዓት ጀምሮ በ____________________*(ጉባዔው የሚካሄድበት ቦታ እና አድራሻ በዝርዝር ይገለጽ)* ይካሄዳል፡፡ በመሆኑም የተከበራችሁ የአክሲዮን ማህበሩ ፈራሚዎች በዕለቱ በጉባዔው ላይ እንድትገኙልን የማህበሩ ________________________ *(ጉባዔው የሚጠራው አካል በግልጽ ይጠቀስ)* ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

## 1. <u>ማህበሩን የሚመለከቱ ዋናዋና መረጃዎች</u>

1.1 የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ(ካፒታል):-___________________________

1.2 የአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ(ካፒታል):-_____________________________

## 2. <u>የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች</u>[16]

2.1 ……………

2.2 ……………

2.3 ……………

## 3. <u>ማሳሰቢያ</u>

3.1 በጉባዔው ላይ መገኘት የማይችሉ ፈራሚዎች ተወካዮቻቹ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠው የውክልና ሠነድ ዋናውንና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የንግድ ሕግ አንቀጽ 377 መሠረት ጉባዔው ከመካሄዱ ከሦስት ቀን በፊት በ____________________*(ቅጹ የሚሞላበት ቦታና አድራሻ ይጻፍ)* በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በአደራጅ ኮሚቴ የተዘጋጀውን የውክልና ቅፅ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባዔው ተካፋይ ለመሆንና ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡ ሆኖም አንድ ፈራሚ በማህበሩ የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ስለመሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

---

[16] በዚህ የአጀንዳዎች ዝርዝር ስር የጉባዔው ድምጽ ቆጣሪዎች መሰየም፣ የጉባዔው ጸሐፊ መመረጥ ወይም መሰየም፣ የጉባዔውን አጀንዳዎች እና የጉባዔውን ቃለ-ጉባዔው ማጽደቅ የሚሉ ጉዳዮች የሥነ-ሥርዓት ጉዳዮች እንደመሆናቸው መጠን በቃለ-ጉባዔው የግድ መካተት ያለባቸው ቢሆኑም ውሳኔ እንደሚያስፈልጋቸው መሠረታዊ አጀንዳዎች ግን በጉባዔው የጥሪ ማስታወቂያ መገለጽ/መነገር የለባቸውም፡፡ ሆኖም ይህንኑ ሀሳብ ባለመቀበል በአጀንዳዎች መልክ ከተያዙ በጉባዔው ቀን ልክ እንደሌሎች አጀንዳዎች በቅደም ተከተላቸው ዝርዝር ውይይት ተደርጎባቸው ውሳኔ የሚሰጥባቸው ስለመሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

3.2 የአክሲዮን ማህበሩ ፈራሚዎች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባዔው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን ወይም ማንነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፍቃድ እና እንደአስፈላጊነቱ የዲጂታል መታወቂያ ዋናውንና ፎቶ ኮፒ በመያዝ በጉባዔው ላይ መሳተፍ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ(ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡[17]

**የ_____________________አክሲዮን ማህበር (በምስረታ ላይ ያለ) ______________**

*(ጥሪ ያደረገው አካል ስም ይጻፍ)፡፡*

የፈራሚዎች ቃለ-ጉባዔ ናሙና

---

[17] ይህ መስፈርት በምስረታ ላይ በሚገኝ የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ አ.ማ፣ የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር አ.ማ እና የባንክ አ.ማ ፈራሚዎችን በአስገዳጅነት የሚጠየቅ ላይሆን ይችላል፡፡